# በትግራይ ተለጣፊ ፍለጋ

በኢትዮጵያ ኣዲሶች ክፍላተ ሃገራት (ክልሎች) የኢህኣዴግን ኣቋምና ፖሊሲ የሚደግፉ ታማኝ ተለጣፊ ድርጅቶች በኣንድ በኩል÷ ነጻ ተቃዋሚ ደግሞ በሌላ በኩል እንደሚገኙ የታወቀ ነው። ኢህአዴግ ተለጣፊ ድርጅቶች የሚፈልግበት ምክንያት የህዝቡን እውነተኛ ፍላጎት የሚወክሉ የምር ተቃዋሚዎች ህዝቡን በአንድ ገንቢና ዘላቂ አቅጣጫ ኣደራጅተው÷ በጉልበት ከያዘው ስልጣን ኣላቀው እንዳያስወግዱት በትርምስ ይከላከሉለት ዘንድ ለመሆኑ ብዙ ምርምር የሚጠይቅ ጉዳይ ኣይ መስልም። ለዚህም ነው ኢህኣዴግ በቀደደው ቦይ ገብተን ከመተራመስና የመከራችን ጊዜ ከማራዘም ይልቅ ከህብረት ባሻገር <u>የኣቋም ውህደት</u> ፈጥረን የህዝባችንን መብት እናስከብር÷ የሃገራችንን ህል ውና እንጠብቅ ስንል ጥሪ ያቀረብነው።

እንግዲህ ሁሉም እንደሚገነዘበው እስካሁን ድረስ በትግራይ ውስጥ የምር ተቃዋሚ ይቅርና ተለጣፊ ድርጅትም ኣልነበረም። ለኢህኣዴግ ኣላስፈለገም ነበርና። ኣምባገነኖቹ የኢህኣዴግ መሪዎች በጸረደርግ ትግል ወቅት በፈጠሩት የፓርቲው (ማሌሊት)ና የስለላው (06) መዋቅር ተማምነው÷ የትግራይ ህዝብ የትምኣይሄድብንም በማለት ተዝናንተው ሲገዙት ቆይተዋል። ህዝቡ ጭቆናው እየመረረው÷

ኑሮ እየከፋው÷ በዛም ላያ እነሱ በጠገቡ ጠገበ ተብሎ እየተወቀሰ÷ ከሁሉም አቅጣጫ ፍትህ ቢያጣ ም፤ በዚያው በተጠናከረ የኣፈና መዋቅር ስር እያለ ተቃውሞውን በብዙ መልክ ማስተጋባት በመጀ መሩና አምባገነኖቹ ሌት ተቀን ከሚያባንን ስጋት ውስጥ በመግባታቸው÷ ካለፈው ኣመት ጀምሮ ኣ ደግዳጊ ካድሮች (እንደነ ኣቶ ህቡር) ኣውሮፓና ኣሜሪካ ድረስ በማሰማራት ታማኝ ተለጣፊ ድር ጅት ለመፍጠር ሲራራጡ ከርመዋል።

የዚህ ሰንካላ ውጥናቸው ማረጋገጫ ሰሞኑን በድርጅታችን የትግራይ ዴሞክራስያዊ ትብብር(ት.ዴ.ት )ስም÷ የድሮ ማህተማችንን በመጠቀም÷ <u>ግልጽ ደብዳቤ</u> በሚል ርእስ÷ ጥር 10 1993 በበተኑት በ ራሪ ወረቀት ለመገንዘብ ችለናል። የድሮ ማህተማችን ይዞ ከድርጅቱ የለቀቀ ግለሰብ ለዚህ ኣሳፋሪ÷ ያው በሌሎች ክልሎች ለተለመደው ከፋፋይ ዘዴኣቸው÷ ኣመቺ ሁኔታ እንዲፈጥርላቸው ያደረጉ መሆኑንም ኣረጋግጠናል። በነገራችን ላይ ግለስቡ በድርጅታችን ስብሰባዎችና ጉባኤ ተገኝቶ አቋሙን እንዲያቀርብ ካለፈው ዓመት ጀምሮ በተደጋጋሚ ተጠይቆ የሸሸ÷ ተለጣፊነት ያማረው ወይም የሚያ ዋጣ የመሰለውና አሁን ወደ ኢህኣዴግ ጉያ ዘው ያለ ፍጡር ነው።

በዚሁ በበተኑት በራሪ ወረቀት ላይ የሰፈሩት ዋና ዋና ነጥቦች ቀጥለን እንጠቅሳለን።

>> *አንዳንድ ግለስቦችና አጋሮቻቸው...በት.ዴ.ት.ስም ... የኢትዮጵያ ህዝቦች እርስበርስ እን ዲጋጩና ... የጦርነት አዘቅት እንዲነከሩ ... ቁልቁላቸውን ማናፋት ጀምረዋል።... እንደከብ ት እንንዳህ፤ እንረድህ፤ ተከተለን፤ ጦርህን አንሳ ... እያሉ ሲዘምሩ ... በሰላም የሚኖረውን ህ ዝብና ሰራዊት አምጽ እያሉ ሲማጸኑ ይሰማሉ።*

*... ሰላምን ማደፍረስ የኢትዮጵያ ህዝቦችን ጥቅም የሚጻረር ከመሆኑ ባሻገር ለእድገትና ለል ማት እሚደረገውን እንቅስቃሴ እንደገና መግታት መሆኑ አከራካሪ አይሆንም።* << ይለዋል።

በቅድሚያ በኢትዮጵያ <u>ሰላም÷ የእድገትና ልማት እንቅስቃሴ ኣለ</u> የሚለው ኣምባገነኑ የኢህኣዴግ ቡ ድን እንጂ በጭቆናውና በተከታታይ ጦርነቶች የተራቆተው ህዝብና በየግንባሩ አሁንም ኢያለቀው ያ ለ ሰራዊት ኣለመሆኑ እያሰመርንበት የሰላም÷ እድገትና ልማት ትርጉም እውቀቱና ሃላፊነት በጎደለ ው መልኩ ባይስተናገድ ይበጃል እንላለን።

ቀጥሎም ከላይ ለተጠቀሰው ውንጀላና ማስመሰል ዝርዝር መልስ ለመስጠት ጊዜ አናባክንም። ከአም ባገነን ይሁን ተለጣፊ÷ ከጽንፈኛ ይሁን አስመሳይ የመጣብንን የፊት ለፊት ትንንቅና የጀርባ ጠለፋ (ተቃውሞ ሁሉ) በአቋም÷ በፕሮግራም÷ በፖሊሲ ደረጃ ብቻ የምንቋቋም መሆናችንን ስንገልጽ÷ በዚህ የትግል መልክ ብቻ ነው ተለጣፊ ይሁን አስለጣፊ÷ ጽንፈኛ ይሁን አስመሳይ ሁሉ አጋልጠን ዘላቂ የህዝባችንን አመኔታ የምንጎናጸፈውና ለዘላቂ ድልም የምንበቃው ብለን የምናምነው። በዚህ የ ትግል ሂደትም ነው *በትግራይ የተለጣፊ ፍለጋ* ሩጫው የምንቃኘው።

በኣምባገነኖቹ ከፋፋይ አመራር ምክንያት ቀውስ ውስጥ በገባችው ኢትዮጵያ ትርምሱ ቆሞ፥ **ሰላምና እርቅ** ተፈጥሮ፥ የጋራ ህገ መንግስት ተነድፎ፥ የህግ በላይነት ተረጋግጦ፥ በዲሞክራሲያዊ ስርኣት መተዳድር ስንጀመር ብቻ ነው ሰላም፥ ዘላቂ እድገትና ብልጽግና ማምጣት የሚቻለው ይላል ት.ዴ.ት። ይህንን ኣቋሙ በፕሮግራም አስፍሮ፥ ፖሊሲ ነድፎ ተግባር ላይ ለማዋል አምባገነኑ ስርአት ከሰፈነበት ጊዜ ጀምሮ ከመሰል ድርጅቶችና ሃገር ወዳድ ሃይሎች ጋር በመተባበር በጽናት ታግለዋል። ወደፊትም በዚህ ኣቋሙ ይዘልቃል።

ድርጅታችን ት.ዴ.ት ከዚህ በፊትም ይሁን አሁን ኢህኣዴግን የሚያውቀው፥

1 ሰብኣዊ መብቶችን የሚረግጥ፥ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን የሚያፍን፥ያለፍርድ የሚያስርና የሚገድል፥
2 ህዝብን በዘር፥በቋንቋ እየከፋፈለና እያጣላ በስልጣን ለመሰንበት እንደ የፖለቲካ ዘዴ የሚጠቀም፥
3 አፍኖ የያዘው የትግራይ ህዝብን እንደደጋፊውና ተጠቃሚ በማስመሰል ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ የሚለያይና በሱ ስር ኣኑሮ ተከላካይ እንዲሆንለት የሚጥር፥
4 ሰላምና እርቅ እንዲሁም ብሄራዊ ውይይት ያስፈልጋል የሚሉትን በጦር ሞክሩኝ እያለ የሚደነፋ የሃገር ፍቅር የራቀው ጦረኛ፥
5 ኢኮኖምያዊ ፖሊሲው የራሱን ፖለቲካ ቡድን ያከበረ፥ ህዝቡን በድህነትና በሽታ ያደቀቀ፥
6 ምርጫ እያለ ህዝቡን የሚያስገድድና ውጭውን ዓለም ለማጭበርበር የምርጫ ትያትር የሚያሳይ፥
7 በህግና ደንብ ሳይሆን በወገንና ጉቦ የሚሰራ፥ ሙስናን ያስፋፋ አምባገነናዊ ቡድን መሆኑ ነው።

ስለዚህ ኢህኣዴግ ይሁን ማንም ነገ የሚተካው ሃይል በዴሞክራስያዊ ስርዓተ መንግስት ካላመነና ለህ
ዝባዊ ውሳኔ ተገዢ ካልሆነ ዘላቂ ሰላም፥ እድገትና ልማት ያመጣል ማለት ቁንጹል ኣስተሳሰበ ከ
መሆኑ ባሻገር የህዝቡን ጎስቋላ ኑሮ እንዲቀጥልና ሃገሪቱ ካለችበት አሳዛኝ ሁኔታ ፈቅ እንዳትል ገ
ብቶትም ይሁን ሳይገባው ኣሉታዊ ኣስተዋጻኦ የሚያደርግ ነው።

እነዚሁን የት.ዴ.ት (TAND) አቋሞችን የማያንጸባርቅ ማንኛውም በት.ዴ.ት ስም የሚበተን ጽሁፍ የኢህኣዴግ ተለጣፊ እንጂ የድርጅታችን ኣለመሆኑ እየገለጽን፥ ወደፊት የሚወጡ ጽሁፎችም እዚህ ላይ ኮለል ብለው በተቀመጡት ኣቋሞቻችንና ከነዚሁ ኣቋሞች በሚመነጩ ፖሊሲዎች ኣንጻር ተለይቶ እንዲታይልን እናሳስባለን።

የኢህኣዴግ ገዢ ቡድን በጠገበና በተመቸው፥ ህዝቡ በእድገትና ልማት እንቅስቃሰ ላይ ነው፥ ሰላም ኣግኝተዋል የሚሉን ወገኖች የሃገሪቱን ኣጠቃላይ ቀውስና የህዝቡ ኣስከፊ የኑሮ ሁኔታ ማየት የተሳናቸው፥ እራሳቸው ኣምባገነኖቹ ኢህኣዴጎችና የነሱን የሙስና ኑሮ የሚቋምጡ ኣቋመ-
ቢስ ኣድርባዮች ብቻ መሆናቸውን ግልጽ ሆኖ እንዲታይልን እንፈልጋለን። የተበደለው ህዝቡ ወገን ነኝ ብሎ የሚያምታታ ሁሉ ከህዝብ ፊት ቀርቦ ኣቋሙን እንዲገልጽም እንጠይቃለን።

ኣሁንም >> የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰላም አግኝተው በእድገትና ልማት እንቅስቃሰ ላይ ናቸው << የ
ሚለው ውዳሴ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ መስፈር የነበረበት የኢህኣዴግ ልፈፋ እንጂ የት.ዴ.ት. ኣቋ
ምሊሆን እንደማይችል መብት፥ ሰላምና እድገት ለተነፈገው የኢትዮጵያ ህዝብና ለሚመለከታቸው ድ
ርጅቶች ደግመን እያረጋገጥን፣ በህዝብ መሰረት የሌለው አምባገነኑ ኢህኣዴግ በተለጣፊ ተንጠልጥሎ
ለመሰንበት በሌሎች ክልሎች እንዳደረገው ሁሉ በትግራይም ተለጣፊ እያበጀ ህዝባችሁን እንዳያተራ
ምሰው እጅ ለእጅ ተያይዘን እንታገለው እላለን።

የኣምባገነኑ ኢህኣዴግ ስርኣት ኣስወግዶ፥
ሰላምና እድገት ልማት ለማምጣት ትግሉ ይቀጥላል! ይቀጥላል! _ _ __

ት.ዴ.ት. (TAND)
የካቲት 1993